Toronto Community
Housing Corporation
931 Yonge Street
Toronto, ON M4W 2H2

Toronto Community Housing

ነሐሴ 3, 2021

ውድ የቲሲኤችሲ ተከራዮች፣

እንደ ፕረዚዳንትና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣን ሆኜ የቶሮንቶ ማሕበረሰብ የቤቶች ጉዳይ ቢሮ በመቀላቀሌ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ኩባኒያው አገልግሎትን ለተከራዮች እንዴት እንደሚሰጥ ለመለወጥ እየተወሰዱ ያሉ ለውጦች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑ ናቸው፣ ስለሆነም በዚህ እና በሌሎች መስኮች የኩባንያውን ቀጣይ እድገት መምራት እፈልጋለሁ፡፡

በሚቀጥሉት ሳምንታት ቅድሚያ የምሰጠው ጉዳይ ቢኖር ማዳመጥ እና መማር ነው፡፡ ሥራዎቻችንን በራሴ ለማየት እችል ዘንድ ከተከራዮችና ከሠራተኞች ጋር ለመገናኘት እኔው ራሴ በቲሲኤችሲ ህንጻዎች፣ በቢሮዎች እና በአዲሱ የተከራይ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ጊዜዬን አጠፋለሁ፡፡ ስለ እርስዎ ያሉት ልምዶች እንዲሁም ለእርስዎ በጣም አስፈላጊ ስለ ሆኑትና ቀደም ሲል በተከናወነው ከባድ ሥራ ላይ ለመገንባት ያሉትን ዕድሎች ለመስማት እፈልጋለሁ፡፡

በካናዳ ውስጥ የትልቁ የማኅበራዊ መኖሪያ ቤቶች አቅራቢ በሆነው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣን ከመሆን ጋር የሚመጣው ኃላፊነት፣ በተለይም በዚህ ጊዜ ማለትም ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ መውጣት እየጀመርን ባለንበት ጊዜ በመሆኑ እጅግ አስገርሞኛል፡፡ የእኛ ተልዕኮ ግልጽ ሆኖ አያውቅም፡፡ ይሁን እንጂ እኛን የሚመራ ጤናማ ስትራቴጂ አለን፣ እንዲሁም የተከራዮች፣ የሠራተኞች እና የአጋሮች ቁርጠኝነትና ፍላጎት ይበልጥ ወደፊት የሚመራን ይሆናል፡፡

ይህንን አዲሱን ሚናዬን ለመጀመር እና እርስዎንም ለማገልገል ወደፊት በጉጉት እየተጠባበቅሁ በእርግጥ ደስተኛ ሆኜአለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር፥

ጃግ ሻርማ
ፕረዚዳንት እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣን
ቶሮንቶ ማሕበረሰብ መኖሪያ ቤቶች